# የዜግነት ክብር

**በዕውቀት የዜግነታችንን ክብር እንጎናፀፋለን!**




የተመሳሳይ ጾታ ፍቅር: ተፈጥሮአዊ ወይስ ኢ-ተፈጥሮአዊ?

ማንነቴን ለምን እጠላለሁ?

የተመሳሳይ ፆታ ተማርኮ በኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ ውስጥ

የተመሳሳይ ጾታ ፍቅር እና አፍሪካ

“የሌዝቢያን ፖርንማ ፀዴ ነው!” ...ወንዶች ስሙኝማ!

FAGulous!



1st Edition | 1ኛ ዕትም
November 2020 | ህዳር 2013



©Yezeginet Kibir | ©የዜግነት ክብር

# በውስጥ ገጾች...


የአዘጋጁ መልዕክት ስለ የዜግነት ክብር — 1

የተመሳሳይ ፆታ ተማርኮ በኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ ውስጥ — በቤን ዶሚኒስ — 2

ዝምታዬን እሰብራለሁ — ግጥም በቤን ዶሚኒስ — 5

ይድረስ ከአካባቢህ ሁሉ የተለየህ ልዩ ፍጥረት የሆንክ ለሚመስልህ ትንሹ እኔ፡ — በቤን ዶሚኒስ — 6

የተመሳሳይ ጾታ ፍቅር: ተፈጥሮአዊ ወይስ ኢ-ተፈጥሮአዊ? — በ ኢትዮ ፍቅር — 7

ከቆምንበት ቦታ — ዕውነተኛ ታሪክ በዴቪድ አብርሃም — 10

የተመሳሳይ ጾታ ፍቅር እና አፍሪካ — በቤን ዶሚኒስ — 12

ማንነቴን ለምን እጠላለሁ? — በቤን ዶሚኒስ — 14

“የሌዝቢያን ፖርንማ ፀዴ ነው!” ...ወንዶች ስሙኝማ! — በቤን ዶሚኒስ — 17

FAGulous! by Victor Geta — 20

Poetry Collection by Yona — 21

General Information — 22



**የዜግነት ክብር ...**

የምናውቀው ፣ የተማርነው ፣ የምናየው ... “ወንድ እና ሴት” ... የሚሰማን ግን ሌላ ሆኖብን ግራ የገባን ጊዜ ፣ ባልመረጥነው ለነገሮች ባለን ተፈጥሮአዊ ስበት ምንክንያት መጠቋቆሚያ ሆነን አንገታችንን አቀርቅረን ከመሬት ጋር እንድትውጠን ሙግት የገጠምን ጊዜ፣ መሳይ እና መልስ ፍለጋ የቃተተች ነፍስ ውጤት ናት እንግዲህ፡፡

**ክብር ለሁላችን!**

●●●

**Yezeginet Kibir...**

For all the time and pieces of ourselves we have lost fighting inside against what we know, feel, been taught and see;

For all the days we put our heads down because of the way we are, and yearning for something to look up to!


ቤን ዶሚነስ
Ben Dominus



**አዘጋጅ**
የዜግነት ክብር

**ዋና አዘጋጅ**
ቤን ዶሚነስ

**ዲዛይን**
የዜግነት ክብር

**ተሳታፊዎች**
ቤን ዶሚነስ
ኢትዮ ፍቅር
ቪክተር ጌታ
ዴቪድ አብርሃም
ዮና

**ልዩ ምስጋና**
ዳንኤል ስኮት
ዊሊ ብሮ
ቦቼ ቢኖ



©
**የዜግነት ክብር**



**1ኛ ዕትም**
**ኅዳር 2013**


Like | Follow | Subscribe
/yezeginetkibir
Click

https://theyezeginetkibir.wordpress.com/

# የተመሳሳይ ፆታ ተማርኮ በ ኢ ት ዮ ጵ ያ ስነ-ፅሁፍ ታሪክውስጥ


በቤን ዶሚነስ



እ.አ.አ በ ኦክቶበር 05 2013 አዲስ አድማስ ጋዜጣ በጥበብ ዓምዱ በአምደኛው ወ/መድህን ብርሃነመስቀል ፀሐፊነት “የአማርኛ ልቦለዶችና የግብረሰዶም ባህሪ ማቆጥቆጥ” በሚል ርዕስ አንድ ዘገባ አውጥቶ ነበር፡፡ ፅሁፉ ለአንድ የግል ኮሌጅ የመመረቂያ የተዘጋጀ ጥናትን ተመርኩዞ እንዴት የተለያዩ የተመሳሳይ ፆታ ፍቅርን የሚያትቱ ታሪኮች በተለያዩ ኢትዮጵያዊ የሆኑ እና በኢትዮጵያውያን የተፃፉ ልብ ወለዶች ውስጥ እንደተካተቱ ያስታውሳል፡፡

በተለይም በ1963 የተፃፈው የኃይለ ሥላሴ ደስታ “የሚያቃጥል ፍቅር” ፣ የ1952ቱ የታደሰ ሊበን “ሌላው መንገድ” እንዲሁም የስብሐት ገብረእግዚአብሔር “ማስታወሻ” (በደራሲ ዘነበ ወላ የተዘጋጀ) የተባሉ ልብወለድ ስራዎች በአገራችን የተመሳሳይ ፆታ ፍቅር እንደ አሁኑ በደንብ አይታወቅ እንጂ ከግማሽ ክ/ዘመን በፊት ይተረክ እንደነበር የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

**“የአማርኛ አጭር ልቦለድ ጀማሪ ተብለው ከሚጠቀሱት ደራስያን አንዱ የሆነው ታደሰ ሊበን በ1949 ዓ.ም “መስከረም”፣ በ1952 ዓ.ም “ሌላው መንገድ” የተሰኙ ሁለት የአጫጭር ልቦለድ መድበሎች ያሳተመ ሲሆን ደራሲው በኢትዮጵያ ውስጥ የግብረ ሰዶማውያንን ሁኔታ የሚያመለክት ጭብጥ በማንሳት ፈር ቀዳጅ እንደሆነ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር በ2000 ዓ.ም ያሳተመው ደራሲያንን የሚያስተዋውቅ አውደ እለት (አጀንዳ) ይጠቁማል፡፡**



**“ሌላው መንገድ” ስድስት አጫጭር ልቦለድ ታሪኮችን ያካተተ ሲሆን፤ በመጽሐፉ ከገጽ *55* እከ *74* የሚዘልቀው ታሪክ ዋና ገፀባሕሪ፣ ብርሃኑ የሚባል የ*22* ዓመት ወጣት ነው። ታሪኩን “እኔ” እያለ በአንደኛ መደብ የሚተርከው ገፀባህሪ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የደንበኞች ቼክ ክፍል ውስጥ ነው የሚሰራው።**

**ከቁመቴ ማጠር በስተቀር ደም ግባቴ በጣም ቆንጆ ነበር። ይህንንም በየዕለቱ የተለያዩ ሰዎች በተለይ ሴቶች የሚያረጋግጡልኝ እውነት ነበር የሚለው ብርሃኑ፤ መልከመልካምነቱን ሲገልፅ፤ “ቀጥ ያለ አፍንጫ፣ ትክክል የሆኑና ንጣታቸው በረዶ የመሰሉ ጥርሶች፣ እጅግም ያልወፈሩ እጅግ በጣም ያልሳሱ መካከለኛ ከንፈሮች፣ ቅንድቦቼ የተኳሉና የተቀነደቡ የሚመስሉ፣ ፀጉሬ፣ ግንባሬ፣ ጉንጮቼ፣ ጆሮዎቼ፣ እምንም ዘንድ ያልተዛቡ፤ በጠቅላላው የሰራኝን እጅ ረቂቅነት አጉልተው የሚያወሱ ነበሩ። ለሴቶችም የማይችሉት ፈተና ነበርኩ...ሲያዩኝ መተርከክ፣ ማተኮር፣ መገላመጥ ግዴታቸው ነበር።”**

**ጥሩ መልበስ ውበቴን ስለሚያጐላው አልባሌ ነገር መልበስ አዘውትር ነበር የሚለው ዋና ገፀ ባሕሪ፤ በ1942 ዓ.ም እለተ ሰኞ የገጠመውን ይተርካል። በቼክ ክፍል ለመገልገል የመጡ አንድ ደንበኛው ካስተናገዳቸው በኋላ፣ ለአንድ ጉዳይ እንደሚፈልጉት በመግለፅ እቤታቸው እንዲመጣ ይቀጥሩታል።**

**ሰውየው በትልቅ ቪላ ቤት ውስጥ ነዋሪ ናቸው። የግቢ ጠባቂ ዘበኛ፣ የእልፍኝ አስከልካይ ወንድና ሴት አገልጋዮችም አሏቸው። መኖሪያ ቤታቸው ዘመናዊና በውድ ዕቃዎች የተሞላ ነው። ቀጠሮ የሰጡት ወጣት ሲመጣ፣ ውስኪ እየጋበዙ ያጫውቱት ጀመር። የእጅ ሰዓት ከኤደን (የመን) እንደሚያመጡለት ቃል ገቡለት። ሁለት ሙሉ ልብስ የሚያሰፋበትን ጨርቅ በአቅራቢያው ካለው ሱቅ እንዲወስድም ነገሩት። ከዚህ በኋላ ነው ጉዱ የመጣው። “ሁሉ ሰው፣ መቼም ተፈጥሮ ሆኖ አንዳንድ አመል አለው” በማለት ፍላጐታቸውን በግልጽ ነገሩት። በቀረበለት ጥያቄ ግራ የተጋባው ብርሃኑ፤ “ምንም አልመለስኩለትም፤ ብቻ... አመዴ ቡን ብሎ ኩምሽሽ አልኩኝ”**



ይላል - የገጠመውን ሲተርክ። ከዚያም በብልሃት ከሰውየው ወጥመድ አምልጦ መውጣቱን ይተርካል።
ነገሩ ከተከሰተ ከስድስት ወር በኋላም ሰውየው ተመሳሳይ ጥያቄ ለጓደኛው እንዳቀረቡለት ነግሮን ነው ታሪኩ የሚጠናቀቀው።”

አዲስ አድማስ ይዞት የወጣው ዘገባ የተመሳሳይ ፆታ ፍቅርን እንደ “ከውጭ አገራት የመጣ አፈንጋጭ ልማድ” አድርጎ ቢስለውም እነዚህ ደራስያን በተለይም ኃይለሥላሴ ደስታ “በሕብረተሰቡ ውስጥ ካየውና ከሰማው በመነሳት” ይሔንን መፅሐፍ እንደፃፈው ይናገራል።

ይህን ዘገባ ዛሬ ላይ ሆኜ ሳነበው ፣ በልጅነቴ ያደግሁበት አካባቢ ይኖር የነበረ አንድ ሰው ትዝ አለኝ፡፡ ይህ ሰው በአካባቢው ሰዎች ዘንድ በሥነምግባሩ እና በማህበራዊ ሕይወቱ ተቀባይነት የነበረውና ተወዳጅ የነበረ ሰው ነበር፡፡ ከጎረቤቶቹ ጋር መልካም ቅርርብ ያለው ፣ ሰርግ ወይም ለቅሶ ሲኖር በጉልበትም ሆነ በሀሳብ ለማገዝ ቀድሞ የሚገኝ ፣ ከቤተክርስቲያን የማይጠፋ ፣ ትልቁንም ትንሹንም በትህትና የሚቀርብ … በሁሉ የሚወደድ ነበር፡፡ ከአንድ ነገር በቀር፡፡ ከጀርባው ከሚወራበት “የግብረሰዶም” ባህሪው፡፡

የአካባቢው ሰው በዚህ ሰው መልካምነት ተገዝቶ አያግልለው እና አይጥላው እንጂ ፣ ከጀርባው ግን በ”ግብረሰዶምነት” ይታማ ነበር፡፡ ሚስት አለማግባቱን እና ልጅ አለመውለዱን ተከትሎ ሽማግሌዎች ትዳር እንዲይዝ ቢወተውቱት እና የተለያዩ ሴቶችን ለሚስትነት ቢያስተዋውቁትም እርሱ ግን በላጤነት ኑሮውን መግፋቱ ሰዎቹን ስለ እሱ የበለጠ ለማወቅ እንዳነሳሳቸው አስታውሳለሁ፡፡ እርሱን ለመቅረብ ፣ ግላዊ ህይወቱን ለማወቅ እና ምስጢራዊ እሱነቱ አነሳስቷቸው ራሳቸውን አሳልፈው ወደሱ የተሳቡ ብዙ የሰፈር ሴቶች ነበሩ፡፡ ሁሉንም ግን ባዶ እጃቸውን ነበር የመለሳቸው፡፡ ይህ ተደጋጋሚ የሴቶቹ ሙከራ እና የአንዳንድ ታላላቆች ጥርጣሬም ነበር የእርሱን “ግብረሰዶማዊነት” ሐሜት ያስነሳው፡፡ ከዛም በኋላ ቢሆን ግን ከጀርባው ከማውራት ባለፈ ፣ ማንም አግልሎት ወይም በግልፅ ተናግሮት አያውቅም ነበር፡፡

የተመሳሳይ ፆታ ተማርኮ ያላቸው ሰዎች የሕብረተሰቡ አካል ናቸው ፤ ነበሩ ፤ ወደፊትም መሆናቸውን ይቀጥላሉ፡፡ በባህል እና በኃይማኖት ምክንያት የሆነ ጊዜ ላይ ተሸሽገው ፣ ራሳቸውን ደብቀው ወይም እንዲደብቁ ተገድደው ሊቆዩ ይችሉ ይሆናል እንጂ፡፡ ምንም ያህል ብንሸፋፍነው እና ባዕዳዊ አንድምታ ብናላብሰውም እነዚህ ቀደምት የስነፅሁፍ ስራዎችም ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡

# ዝምታዬን
# እሰብራለሁ

(ከ This Is Me : (a song by Keala Settle) በውርስ የተተረጎመ)

ለድቅድቁ ፅልመት እንግዳም አይደለሁ
“ሰባራነትህን አንፈልግም ልናይ ጥፋ” ተብያለሁ
ሀፍረትን ተማርኩኝ የገላዬን ሰንበር ግርፋት እያየሁ
“ጥፋ ከፊታችን ማንም አይወድህም” ብለው ሰድደውኛል
እኔን እንድጠላ ጠልተው መክረውኛል


ግን አልሰበርም አልፈቅድላቸውም እንዲያደቃቅቁኝ
ዛሬ ባይሆን ነገ ፣ አሁን ባይሆን ኋላ ለኔም ቦታ እንዳለ በእርግጥ አውቃለሁኝ
ቀና ብዬ ብሄድ አሸንፋለሁኝ

ቃላቶች ተስለው ሾለው ቢመጡብኝ
አከላቴን ዘልቀው ስሜቴን ሊጎዱኝ
አልፈቅድላቸውም : ጋሻዬን አንስቼ እመክታለሁኝ
ወኔ አለኝ የራሴ የሰውነቴ ኃይል
ብቆስል ብጫጫር ማንነቴን አልተው ወደኋላም አልል
ቀና በል ጠዪዬ እየኝ ሳንሰራራ
በመንፈስ ጠንክሬ በራሴ ስደሰት በራሴ ስኮራ
ከመታየት ላልሸሸ ራሴን ስገልጥ ራሴን ስጠራ
ይቅርታም ሳልጠይቅ በእኔነቴ ሳላፍር መልካሙን ሳፈራ

እርግጥ ነው

ጥይትህ መትቶኛል ደጋግሞ ደጋግሞ ሰውነቴን በስቷል
አሁንም ተኩሰው ዛሬ ላልደበቅ በራሴ ምያለሁ ሀፍረት ከኔ ርቋል
መሰናክሎችህን ሰባብሬ አልፋለሁ ብርሃን ብዙ አይርቅም
ከጨለማ አምልጬ ፍንጣቂ አያለሁ ተስፋዬም አይደርቅም
እመነኝ ጥላቻህ ጠንካራ አድርጎኛል ዳግም አትሰብረኝም!

(ቤን ዶሚነስ)



# ይድረስ ከአካባቢህ ሁሉ የተለየህ ልዩ ፍጥረት የሆንክ ለሚመስልህ ትንሹ እኔ፡

(ቤን ዶሚነስ)

እውነት ነው የተለየህ ነህ። ልዩነትህ ግን አንተ እንደሚሰማህ መጥፎ ልጅ ፣ የተረገምክ ወይም ሰይጣን ስለያዘህ አይደለም። የተለየህ የሆንከው እስካሁን ባሳለፍካቸውና ከዚህ በኋላም በህይወትህ ከሚያጋጥሙህ አካባቢያዊ መሰናክሎች እና ውስጣዊ ትግሎች ውስጥ አልፈህ አሁን ላይ ስላደረስከኝ ነው። ልዩ ነህ።

ከዚህ በኋላ የሚያጋጥሙህ መሰናክሎች እና ትግሎች ስልህ ደግሞ አትደናገጥ። ይኼው የምትፈራው ልዩነትህ ጥንካሬንና ትዕግስትን በደንብ ስለሚያስተምርህ ፣ አንዳንዴ ብትጎዳም ግን ታልፈዋለህ። አንተነትህን ብቻ አትሳት።

በዕድገትህ ብዙ መልካምም መጥፎም ነገሮች ይገጥሙሃል። ብቻህን የሆንክ እስኪመስልህ ድረስ ያለህበት ግራ መጋባት ገና የቤተሰቦችህ ፣ የኃይማኖትህ ፣ ብሎም የሌሎች የምታውቃቸውም ሆነ የማታውቃቸው ሰዎች በአንተነትህ ላይ ባላቸው አመለካከት ሊሰብርህ ይሞክራል። ዕውነት ለመናገር ማንነትህን በደንብ ስትረዳው ገና አሁን ካለህበት ግራ መጋባት የበለጠ ከራስህ ጋር ጦርነት የምትገባበት ጊዜ ይመጣል። የቱ ትክክል ፣ የቱ ስህተት እንደሆነ የማታውቅበት ፣ በራስህ እንድታፍር የምትገደድበት ፣ በሌላ ማንነት ውስጥ ተሸሽገህ ዕውነተኛ አንተነትህን በውስጥህ ቆልፈህበት ማስመሰልን የምትማርበት ጊዜም ይመጣል። ግን ታልፈዋለህ። ጠንካራ ነህ።

ይኼንን ነገር አታድርግ ፣ ይኼንን ነገር አድርግ እያልኩ አልጨቀጭቅህም። ያደረግካቸውም ያላደረግካቸውም ነገሮች ጥንካሬህን የምትማርባቸው ፣ ህይወትን የምትለምድባቸው ፣ ሳትጠይቅ ነህ የተባልከውን ማንነት ተጋፍተህ ራስህን የምታገኝባቸው የህይወትህ ትምህርቶች ይሆናሉና አትፍራ።

አንድ በጣም ቀላል ነገር ግን ትልቅ ዕውነት ልንገርህ። አንተነትህ ፣ ያንን የጎረቤታችንን ልጅ ስታየው የሚያስቅ ...ግን ደስ የሚል ዓይነት የሚሰማህ ስሜት ፣ ወንዶች ጓደኞቻችን ተሰብስበን ስለ ሴቶች ጓደኞቻችን ሲያወሩ ብዙም የማይመስጥህ ነገር .... ስህተት አይደለም። እመነኝ ... አልፌበታለሁ ... አውቀዋለሁ።

ምናልባትም በዚህ ልዩነትህ ብቻ ብዙ ሰዎች ምቾት ላይሰማቸው ፣ አልፎ ተርፎም በቃላትም ሆነ በአካል ሊያጠቁህ ይችላሉ። ምክንያታቸው ብዙ ነው ... እያደግህ ስትሄድ እየተረዳኸው ትመጣለህ። ነገር ግን እነሱን ማስደሰት ፣ የእነሱን ሃሳብ ማሟላት ያንተ ግዴታ አይደለምና ብዙም አይረብሽህ። ራስህ ላይ ብቻ አተኩር ... ራስህን አስቀድም።

ስታድግ ብዙ የሚወዱህ እና የምትወዳቸው ሰዎች ያጋጥሙሃል። በአንተነትህ ፊታቸው ሳይጨማደድ እቅፎቻቸውን ከፍተው የሚቀበሉህ አንተን መሳይ ሰዎች ትተዋወቃለህ። ፊታቸውን የሚያዞሩብህም አይጠፉም ... ለነዚህ ብዙም ትኩረት አትስጣቸው።

ብዙ ብዙ የምነግርህ ነገሮች አሉኝ። ምናልባት ሌላ ጊዜ እፅፍልህ ይሆናል። ለዛሬ ግን አንድ ነገር ብዬህ ላብቃ።

ያ ተደብቀን ስናየው ደስ ደስ የሚል ስሜት እንዲሰማን የሚያደርገን የጎረቤታችን ልጅ .... አታገኘውም! አርፈህ ተቀመጥ። (ሳቅ እንጂ )

የ ሠላሳ ምናምን ዕድሜው አንተ።

-------------

ቤን ዶሚነስ

# የተመሳሳይ ጾታ ፍቅር
## ተፈጥሮአዊ ወይስ ኢ-ተፈጥሮአዊ?

በ ኢትዮ ፍቅር

የተመሳሳይ ጾታ ፍቅርን በመቃወም በርካታ የመከራከሪያ ነጥቦች ይቀርባሉ። ክርክሮቹ በአብዛኛው ለተመሳሳይ ጾታ ካለ ጥላቻ የሚቀርቡ ቢሆንም የተወሰኑት ግን የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ምንነትን ለማወቅ ከሚደረግ ሙከራ የሚመነጩ ናቸው። አብዛኞቹ ክርክሮች አመክንዮ የጎደላቸው ፤ ከሳይንስ እና መሰረታዊ እውቀት የተጣሉ ሲሆኑ ጥቂቶቹ ደግሞ መጠነኛ የእውነት ቅመም ከብዙ መላምት እና ሀሰተኛ መረጃ ጋር አደባልቀው የያዙ ናቸው።ዞሮ ዞሮ እነዚህ ሀሳቦች በስህተት የተሞሉ ቢሆንም የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ምንጭ ናቸውና ከመደጋገም ብዛት የመታመን እድል ይኖራቸዋል። በተለየም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሳይንስ እና አመክንዮ ቦታ እንዳያገኙ በትጋት በሚሰራባቸው ሀገራት ሰዎች የራሳቸውን ውሸት የማመን እድላቸው ሰፊ ነው። ከእነዚህ የመከራከሪያ ነጥቦች የመጀመሪያው እና ዋነኛው “የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ኢ ተፈጥሮአዊ ነው።” የሚለው ነው።

“የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ኢ ተፈጥሮአዊ ነው”
በመጀመሪያ ተፈጥሮአዊ እና ኢተፈጥሮአዊ ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን መለየት አስፈላጊ ነው። ተፈጥሮአዊ ማለት የሰው ልጅ ራሱ ያልሰራው እና በፈቃዱ ሊቀይረው የማይችለው ማለት ነው። ኢ ተፈጥሮአዊ ማለት ደግሞ ሰው ሰራሽ ማለት ነው። በዚህም መሰረት የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ ተፈጥሮአዊ ነው ወይ? ብለን ስንጠይቅ መልሱ አዎ ነው። ማስረጃዎቹም ብዙ ልንልባቸው የምንችላቸው ስነ አካላዊ/ባዮሎጂካል/ ዕውነታዎች እና ማብራሪያወች ናቸው።
ኢ ተፈጥሮአዊ ነው ወይ? ብለን ስንጠይቅ ደግሞ መልሱ አይደለም ነው የሚሆነው። ማንም ሰው በፈቃዱ ከቤተሰቡ ፤ ከማህበረሰቡ ፣ ከሀይማኖቱ ፣ ከባህሉ ጋር ፍጥጫ ውስጥ መግባት አይፈልግም። እርግጥ ነው ሰው በተለያዩ ምክንያቶች ከራሱ ፣ ከአካባቢው ፣ ከቤተሰቡ ፣ ከማህበረሰቡ ፣ ከሀይማኖቱ ፣ ወዘተ ጋር ...ይጋጫል። ለምሳሌ በሱስ ምክንያት ብዙ ወጣቶች ተመሳሳይ ግጭት ውስጥ ገብተዋል። ሆኖም ሱስ ግን በህክምና ሊስተካከል የሚችል ነው። የተመሳሳይ ጾታ ዝንባሌ በህክምና ሊስተካከል አይችልም። እስካሁን የትኛውም ሀይማኖትም ሆነ ሳይንስ ይህን አስተካክሎ አልታየም። በሳይንስ በዙ የተራመዱትም ሆነ በሀይማኖት የተራቀቁት ተፈጥሮአዊ የሆነውን የተመሳሳይ ጾታ ፍቅር መቀየር አልቻሉም። የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎችን ወደ ተቃራኒ ጾታ እንዲያዘነብሉ የተደረገው ጥረት ተፈጥሮን ከማስተካከል ይልቅ የበለጠ ከተፈጥሮ የሚያርቅ ሆኖ ተገኝቷል።

ወደ ቀደመ ጉዳያችን ስንመለስ ይህን ክርክር የሚያነሱ ወገኖች ብዙውን ጊዜ በሁለት ይከፈላሉ። አንደኞቹ ሀይማኖተኞች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ሀይማኖተኛ ያልሆኑ ናቸው።

በመጀመሪያ ሀይማኖተኛ ወዳልሆኑት እንመልከት።
እነዚህ ለተቃውሞአቸው ማስረጃ የሚያረጉት የራሳቸውን የተፈጥሮ ትርጉም ነው። የወንድ ብልት የተሰራው ከሴት ልጅ ብልት ጋር እንዲገጥም ሆኖ ብቻ ነው ይላሉ። የዚህ ክርክር ስህተቱ ተፈጥሮን ከወሲብ ጋር ብቻ ማስተሳሰሩ ነው። የወንድ ልጅ ብልት ከሴት ልጅ ብልት ጋር ብቻ ይገጥማል ብንል እንኳን የወንድ ልጅ ልብ ከሌላ ወንድ ልብ ጋር አይገጥምም ማለት አይቻልም።

ሁለተኛ ሁሉም ወሲብ ሰጪና ተቀባይን/penetration/ ያማከለ አይደለም። ሰጪና ተቀባይ / አድራጊ እና ተደራጊ/ ከሌለ ወሲብ የለም ማለት ወሲብን በጠባብ አውድ መረዳት ነው።

ሶስተኛ በመቀመጫ የሚደረግ ወሲብ እርካታ እንደሚሰጥ ተፈጥሮ ያስረዳል ፣ ሳይንስም አረጋግጦታል። ከዚያ ባለፈ መቀመጫችን ለመጸዳዳት እንጂ ለወሲብ አልተፈጠረም ለሚሉ ብልታችንም ለመጸዳዳት እንደሚያገለግል ማስታወስ በቂ ነው። የወንድም ሆነ የሴት ብልት ለወሲብ ከተጠቀምንበት ጊዜ ይልቅ ለመጸዳዳት የተጠቀምንበት ጊዜ ይበልጣል። መቀመጫ መጸዳዳት ብቻ ነው ስራው ማለት አፍ መብላት እና ማውራት ብቻ ነው ስራው ለምን እንሳሳምበታለን እንደማለት ነው።

እርግጥ ነው የሴት ልጅ ብልት ለወሲብ የሚያመነጨው እና በወንዶች ዘንድ የማይገኝ ፈሳሽ አለ። ያ ፈሳሽ ግን ሴት ልጅ ከወንድ ጋር ብቻ ሳይሆን ሴት የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን (ሌዝቢያን) እርስ በርስ ወሲብ ሲያደርጉ የሚመነጭ ነው። የሴት ብልት በተለያዩ ምክንቶች ይህን ፈሳሽ የማያመነጭባቸው ጊዜያት አሉ።

ለምሳሌ ያህል ሴቷ ወሲብ እያደረገች ካለችው ወንድ ወሲባዊ መነሳሳት ካጣች ይህ ፈሳሽ ላይመነጭ ይችላል። ስለዚህ ፈሳሹ ለአእምሮአዊ ትእዛዝ የሚሰጥ አካላዊ መልስ እንጂ በራሱ ወንድ ባየ ቁጥር የሚፈስስ ጎርፍ አይደለም። ሴቷ ሌዝቢያን ከሆነች የምትስባትን ሴት ስታይ ብልቷ ይህን ፈሳሽ ያዘጋጃል ፣ የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ከሆነች ደግሞ የሚስባትን ወንድ ስታገኝ ብቻ መመንጨት ይጀምራል።ምርጫዋን የሚወስነው አእምሮዋ ነው። አካሏ ግን ለዚያ መልስ ሰጪ ነው። ምርጫዋ ካልሆነ ሰው ጋር ወሲብ ስታደርግ ግን ይህን ፈሳሽ ሊያመነጭ አይችልም።

ለምሳሌ ሌዝቢያን ሴት ከወንድ ጋር ወሲብ ስታደርግ ይህ ፈሳሽ ላይመነጭ ይችላል። ይህ ማለት ለሌዝቢያኗ ሴት ከወንድ ጋር የምታደርገው ወሲብ ኢ ተፈጥሮአዊ ነው ማለት ነው። በተመሳሳይ ለተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ሴትም ከሌላ ሴት ጋር ወሲብ አድርጋ ይህ ፈሳሽ እንዲመነጩ ሊጠበቅበት አይችልም። ምክንቱም ለሷ ያ ወሲብ ከተፈጥሮዋ በተቃራኒ በመሆኑ አእምሮዋ ትእዛዝ መስጠት አይችልምና ነው።

በወንዶች መሀከል በሚደረግ ወሲብ ይህን ፈሳሽ ማመንጨት ባይቻልም ያንን ሊተኩ የሚቸሉ ብዙ ሰው ሰራሽ ግብአቶች አሉ። አንዳንድ የተፈጥሮ ጠበቃ ነን የሚሉ ሰዎች ይህን የሰው ሰራሽ ማለስለሻ ጥቅም ላይ መዋል በወንዶች መሀከል የሚደረግ ግንኙነትን ኢ ተፈጥሮአዊነት ለማሳየት ለመከራከሪያነት ያቀርቡታል። ይሁንና ሰው ልጅ በዘመኑ ሁሉ ያገኛቸው ጠቃሚ መሰረታዊ ነገሮች ተፈጥሮን በራሱ መንገድ በመጠቀም መሆኑን ካወቅን ይህ ሰው ስራሽ ማለስለሻ የመጠቀም ነገር አያሳስበንም። ሰውነታችንን በሳሙና መታጠባችን ሰውነታችን የራሱ የሆነ የቆሻሻ አወጋገድ ስርአት የለውም ማለት አይደለም። ሰውነታችን በራሱ መንገድ ቆሻሻን ያስወግዳል እኛም ግን በሳሙና እንታጠባለን። በተመሳሳይም ሁለት ወንዶች ማለስለሻ መጠቀማቸው በተፈጥሮአዊ መንገድ ብቻ ወሲብ አይፈጽሙም ማለት አይደለም። ማለስለሻው ባይኖርም ግን ወሲቡ መፈጸሙ አይቀርም። ማለስለሻ ባልነበረበት ዘመን በሙሉ የሰው ልጅ ወሲብ ሲያደርግ ኖሯል። ነገር ግን አሁን ባለንበት ዘመን ማለስለሻውን ጥቅም ላይ በማዋል ወሲብን የበለጠ ቀላል ማድረግ ተችሏል። ማለስለሻ ቅባት መጠቀም የተመሳሳይ ጾታ ወሲብን ኢተፈጥሮአዊ አያሰኘውም። ሴቶች በተለያየ ምክንያት ሰውነታቸው ይህን ፈሳሽ ማመንጨት ሲያቆም ማለስለሻን ይጠቀማሉ። ማለስለሻውን መጠቀማቸው የሚፈጽሙትን ወሲብ ኢ ተፈጥሮአዊ አያሰኘውም።

ወደ ሀይማኖተኞቹ ጉዳይ ስንመጣ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነትን ተፈጥሮአዊ አይደለም ለማለት ድፍረቱን ከየት አገኛችሁት ማለት እንወዳለን። ምክንያቱም በአለም ላይ ያሉት ሁሉም ሀይማኖቶች በየመጸህፍቶቻቸው ከተፈጥሮ ውጭ የሆኑ ነገሮችን የያዙ ስለሆነና አማኞቻቸውም እነዚህን ከተፈጥሮ ውጭ የሆኑ ነገሮች አምነው በመቀበላቸው ነው። ነገሩን በስነ ጾታ አንጻር ብናየው ሀይማኖቶች አስገራሚ ተፈጥሮን የሚጻረር ልማድ እና ህግ እንዳለቸው ማየት እንችላለን። ለምሳሌ ከሁለቱ አበይት ሀይማኖቶች አንድ አንድ ምሳሌ እንይ፤-

በኦርቶዶክሱ እና በካቶሊኩ በኩል ከስነ ጾታ አንጻር ኢ ተፈጥሮአዊ የሚባለው ምንኩስና ነው። ይህንንም ያለው የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን መስራች የነበረው እና ራሱም መነኩሴ የነበረውን ማርቲን ሉተር ኪንግ ነው። እንደ ማርቲን ሉተር ኪንግ እና ተከታዮቹ እምነት የምንኩስና ህይወት ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት የሚለውን አምላካዊ ቃል የሚጋፋ የተፈጥሮንም ስርአት የሻረ ነው። አንድ ወንድ መውለድ እየቻለ አለመውለዱ የፈጣሪን  አላማ የሚጻረር ነው ይላሉ ሉተር እና ተከታዮቹ። ወሲብ አለመፈጸም የሰው ልጅ ተፈጥሮን የሚጎዳ እና ጤናን የሚያውክ መሆኑንም ዘመናውያኑ ሉተራውያን ይሞግታሉ። ለሲኖዶሱ አባላት ገለጻ የሰጠችው የፋሚሊ ወች ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ሌስተርም ይህን የምታምን ነች። ምናልባትም ፊት ለፊቷ ተቀምጠው ዲስኩሯን ለሚሰሙት ጳጳሳት መውለድ እየቻሉ በድንግልና መጽናታቸው ተፈጥሮን የሚጻረር ፤ የፈጣሪን ህግ የሚሽር እና ባህላዊውን ቤተሰብ የሚጎዳ ነው ብላ ብታምንም ያልነገረቻቸው የያዘቻውን አላማ ስለሚያበላሽባት ሊሆን ይችላል።

ሙሰሊሞችን በተመለከተ ኢ ተፈጥሮአዊ የሚባለው የትዳር ህግጋታቸው ነው። ይህን ያለው ደግሞ ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርአ ያእቆብ ነው። ፕ/ር ጌታቸው ሀይሌ በተረጎሙት መጽሀፉ ላይ ያለውን ንግግር ቃል በቃል እነሆ፤

> **እኛ ግን የመሀመድ ትምህርት ከእግዚአብሄር ዘንድ ሊሆን እንደማይችል እናውቃለን። ምክንያቱም የሚወለደው ሰው ወንዱና ሴቱ በቁጥር እኩል ነው። በአንድ የተወሰነ ሀገር ያሉትን ወንዶችና ሴቶች ብንቆጥራቸው አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ትደርሳለች። ስምንት ወይም አስር ሴት ለእንዳንዱ ወንድ አይደርስም። ምክንያቱም አንዱ ከአንዲቷ ጋር ይጋቡ ዘንድ የተፈጥሮ ህግ ታዝዛለች። አንድ ወንድ አስር ሴት ካገባ ሚስት የሌላቸው ዘጠኝ ሰዎች ተርፋሉ። ይህም የፈጣሪን ስርአት እና የተፈጥሮን ህጎች ያፈርሳል።**

እንግዲህ ከላይ እንዳነበብነው የካቶሊኩ መነኩሴ እና በኋላም የፕሮቴስታንት መስራች ማርቲን ሉተር ኪንግ ካቶሊካውያን እና ኦርቶዶክሳውን ለዘመናት የተከተላችሁት እና አሁንም እየተከተላችሁት ያለው የምንኩስና ስርአት ኢተፈጥሮአዊ ነው ብሏቸዋል። ሌላኛው መነኩሴ እና ፈላስፋ ዘርዐ ያዕቆብ በበኩሉ ሙስሊሞች የጋብቻ ስርአታቸው የተፈጥሮን ሚዛን የሚያዛባ ኢተፈጥሮአዊ  ነው ብሏቸዋል። ፕሮቴስታንቱ  ደግሞ በኦርቶዶክሱ እና በሙስሊሙ ከተፈጥሮ የተጣላ ፣ ራስን መግራት የሌለበት እና ቁሳዊ ሀሳቦች የበዙበት ስብስብ ሆኖ ነው የሚታየው። እንግዲህ በወሲብ እና ስነ ተዋልዶ ጉዳይ ሁሉም ይህን የመሳሰሉ የገዘፉ ኢተፈጥሮአዊ ስርአቶችን ቢይዙም የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነትን ግን ኢተፈጥሮአዊ ነው ለማለት ድፍረት አግኝተዋል።

# ከቆምንበት ቦታ

**በዴቪድ አብርሃም**

ዴቪድ አብርሃም ኢትዮጵያዊ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሲሆን፡ በፌስቡክ ገፁ በሚያጋራቸው አስተማሪ እና አዝናኝ ልብወለዶች እና በዕውነተኛ ታሪኮች ላይ የተመረኮዙ ጽሁፎቹ ይታወቃል።



ሐምሌ 2004 ዓ.ም ወልድያ ጨለምለም ብሏል፤ ምሽት አንድ ሰዓት አካባቢ ነው። አጎቴ ቤት መልዕክት እንዳደርስ ተልኬ ከቤት ወጥቼ ታክሲ ወደ'ምይዝበት ቦታ እየተራመድኩ ነው። ከቤታችን ጀምሮ እስከ ታክሲ መያዣ ድረስ ትንሽ ራቅ ይላል። በግምት እስከ አንድ ኪሎ ሜትር ይሆናል።

ጫማዬ ተፈተቶብኝ ጎንበስ ብዬ ጫማዬን አሰርኩና ዞር ብዬ ተመለከትሁ። በቅርብ ልጅ አንድ በእኔ እድሜ ክልል ያለ ወጣት ይከተለኛል። በየመታጠፊያዎቹ በደረስኩ ቁጥር ዘወር ብዬ አየዋለሁ። ይከተለኛል። ፍጥነቴን አቀዝቅዤ እንዲያልፈኝ ስለፈለግሁ ቀስ እያልኩ መራመድ ጀመርኩ። ግን አልፎኝ ሊሄድ አልቻለም። እየተከታተለኝ እንደሆነ እርግጠኛ ሆንኩ። በቂ ብርሃን ስላልነበረ በተደገጋሚ ዘወር እያልኩ ብመለከትም መልኩን በትክክል ማዬት አልቻልኩም። ታክሲ በምይዝበት ቦታ ስደርስ በፍጥነት መራመድ ጀመርኩ። ከኋላዬ የነበረው ልጅ ሩጦ ደረሰብኝ።

"አንዴ!" አለና አስቆመኝ።

"ሰላም ብሮ እንዴት ነሽ?" አለ ከእግር እስከ ራሴ እየተመለከተኝ።

"ሰላም.." አልሁ በሁኔታው ግራ ተጋብቼ

"በሰላም ነው? ታውቀኛለህ? እየተከታተልከኝ ነበር..." አልሁ አስከትዬ

"አንተ አታውቀኝ ይሆናል እኔ በሩቁም ቢሆን አውቅሃለሁ። ግን አሁን ያስቆምኩህ የለበስከው ሸሚዝ ስለተመቸኝ ከዬት እንደገዛኸው ልጠይቅህ ነው..?" አለ ደፈር ብሎ።

ምክንያቱ ውሃ አያነሳም። መሳቅም መናደድም ፈለግሁ። ግና ለደቂቃዎች ያህል ከእሱ ጋር ቁሜ መጋተት ስላልፈለግሁ ሸሚዙን የገዛሁበትን ቦታ ነግሬው በቆመበት ትቼው ባጃጅ ውስጥ ገባሁ። ባጃጅ ውስጥ ሁኜ ስለ ልጁ ማሰብ ማቆም አልቻልኩም። ቀይ ቀጠን ያለ ሁኖ መልከመልካም ልጅ ነው። እሱ አውቅሃለሁ ብሎኛል እኔ ግን ከዛሬ በቀር አይቼው አላውቅም።

በማግስቱ ጓደኞቼ ጋር ከተማ ውዬ ወደ ሰፈር ስመለስ ገና ከባጃጅ እንደወረድኩ ኋይለኛ ዝናብ ያዘኝ። ቅርብ ባገኘሁት መጠለያ ሩጬ ተጠለልኩ። ሆኖም የለበስኩት ቲሸርት በዝናብ ከመበስበስ አላተረፈኝም። በጣም በርዶኛል። ብዙም ሳይቆይ ከኋላዬ ጀርባዬን የሆነ እጅ ሲነከኝ ተሰማኝ። ዝናብ የሚያባሩ የተሰበሰቡ ሰዎች መኖራቸውን እንጂ ማን ማን እንደቆመ አላስተዋልኩም ነበር። ዘወር ስል በስስ የፂም ፀጉሮች የተከበበ ምትሃታዊ ፈገግታ ቀድሞ በአይኔ ውስጥ ገባ። እሱ ነው።...ልጁ! ከአንድ ቀን በፊት ስለ'ለበስኩት ቲሸርት የጠየቀኝ ልጅ.....! በፈጣሪ!....ፈገግታው እንዴት ያምራል!!

"እንዴት ዋልህ አቤል" አለኝ። ደነገጥኩ።

"ስሜን እንዴት ልታውቅ ቻልህ ?" ብዬ መጠየቅህ ፈለግሁ። ግን አልቻልኩም። ምክንያቱም በርከት ያሉ ሰዎች ተሰብስበው ነበር። ሰላምታውን መልሼ ሌላ ምንም ነገር ሳልል ቆምኩ። በድጋሜ ጀርባዬን እጅ ሲነካኝ ተሰማኝ፤ ዞርኩ። ራሱ ነው። ጃኬቱን አውልቆ እያቀበለኝ ነበር።

"በጣም በርዶሃል...እኔ ከውስጥ ሹራብ ስለ'ለበስኩ አንተ ይሄን ደርብ" አለኝ። ከንፈሮቹ ሳይሸሹ ጥርሶቹ እንኳን ሳይገለጡ በአይኑ መሳቅ ይችላል። የሚስቁ ውብ አይኖች በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ አየሁ። ጃኬቱን አለመቀበል አልቻልኩም። ተቀብዬ ለበስኩት። ጃኬቱንም ውብ ጠረኑንም ደርቤ ለበስኩ። "ምን አይነት ሽቶ ወይም ዲዮድራንት ይሆን የሚጠቀመው?" አልኩ ለራሴ። በጣም ደስ ይላል። ዝናቡ አባርቶ ሰው መንቀሳቀስ ሲጀምር ጃኬቱን ልመልስለት ማውለቅ ስጀምር ከለከለኝ።

"ስለማታውቀኝ ነው እንጂ አንድ ሰፈር ነው የምኖረው....በቅርብ ነው ወልድያ የገባሁት። የደሴ ልጅ ነኝ። እናንተ ሰፈር አጎቴ ቤት የምኖረው። እኔ በማዬት አውቅሃለሁ...." አለ እየተራመድን። ስሜን እንዴት ሊያውቅ እንደቻለ ጠየቅሁት። ሰፈር ውስጥ ሲጠሩኝ ሰምቶ እንደሆነ ነገረኝ። የእሱን ስም ጠየቅሁት "ቃለአብ" አለኝ። ስለተለያዩ ነገሮች እያነሳን እያወራን ሰፈር እኛ ቤት ደረስን። በድጋሜ ጃኬቱን ለመመለስ ማውለቅ ስጀምር ከለከለኝ። "አንተ ያቆሸሽከውን ማን ይለብሳል...አጥበህ መልስ።" ብሎ እየሳቀ በቆምኩበት ጥሎኝ ሄደ።

ወደ'ቤት ገብቼ እሱን ማሰብ ማቆም አቃተኝ። ትህትናው ውበቱና ፈገግታው በየተራ በአዕምሮዬ እየተመላለሰ ሰላም ነሳኝ። አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ከቤት ወጥቼ ደጅ ቆምኩ። ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ ቃላብን ሲመጣ አየሁት። ሰላም ተባብለን ወክ ማድረግ ጀመርን። በየቀኑ እየተገናኘን ወክ እያደረግን አንድ ሳምንት አለፈ። ባንነጋገርም በስሜት ተግባብተናል። ደፍሮ ሰለማንነታችን የሚናገር ሰው ግን ከመሃላችን ጠፋ።

ከአንድ ሳምንት ጓደኝነት በኋላ አንድ ቅዳሜ ቀን ላይ ደውሎ አግኝቶኝ የሆነ ነገር ሊነግረኝ እንደሚፈልግ ነገረኝ። አዳጎ በሚባለው የከተማው አካባቢ አንድ ሁለታችንም በምናውቀው ካፌ ተቀጣጠርን። ምን ሊነግረኝ እንደሚችል ገምቻለሁ። በዓይነ ህሌናዬ ብዙ ነገር ይታዬኝ ጀመር። ከ ቃላብ ጋር በፍቅር ውብ ጊዜያትን ስናሳልፍ ፥ ጥሩ ጓደኛሞች ስንሆን ታዬኝ። ሙሉ ሰውነቴ በደስታ ሰከረ። አላስችል ብሎኝ የቀጠሮው ሰዓት ከመድረሱ አንድ ሰዓት ቀደም ብዬ ቦታው ላይ ተገኘሁ። ካፌው በረንዳ ላይ ተቀምጬ ቁልቁል አዳጎ አደባባይን እመለከት ጀመር። ቅዳሜ ስለሆነም ጭምር ሰውም ባጃጁም ይተራመሳል።

የቀጠሮው ሰዓት ደረሰ። ቃለአብ ደወለ። እንደደረሰ ነገረኝ። በዚያው ቅፅበት ከላይ ሆኜ ቃለአብን ከሩቅ ተመለከትሁ። በጣም ዝንጥ ብሏል። በአይኖቼ እየተከታተልኩት ነው። አስፓልቱን እያቆረጠ እያለ ነጭ ፒክአፕ መጥታ ቃለአብን ከእይታዬ ስታጠፋው ህልም ላይ ያለሁ መሰሎኝ አይኔን ጨፍኜ ገለጥኩ። አይኖቼን ስገልጥ አስፓልቱ በሰው ተሞልቷል። ባለሁበት ደነዘዝኩ።

ግማሽ ደቂቃ ቆይቼ ጮኹ! ካፌው ውስጥ የተቀመጠው ሰው ሁሉ ወደ እኔ ተራመደ። አይኖቼን ተከትለው ወደ አደባባዩ ተመለከቱ። ተነስቼ እየሮጥኩ ከፎቁ ወረድኩ። በምን ፍጥነት ግጭቱ ቦታ እንደደረስኩ አላውቅም። ነፍሴ ከስጋዬ ተለያይተው የምንሳፈፍ ይመስለኛል። የሰው ከንፈር ምጥጫና ሹክሹክታ ትንሽ ትንሽ ይሰማኛል። ከዚያ ራሴን ያገኘሁት ሆስፒታል አልጋ ላይ ነበር። "አይዞህ!" አለቺኝ አንዲት አጭር ነርስ ገና ከመንቃቴ። መኪና ስለገጨው ወጣት ጠየቅኋት። እንዳረፈ አይኗ በእንባ ተሞልቷ አረዳቺኝ።

ቃለአብ ላይመለስ ሄዷል። እንደገና ሰው ሆኜ ለመቆም ወራት ፈጅቶብኛል። ጃኬቱ ቁምሳጥኔ ውስጥ መኖሩም ያስተዋልኩት ከሶስት ወር በኋላ ነበር። ጃኬቱን ያገኘሁ ቀን እንደገና ታመምኩ። ግን ምን ማድረግ ይቻላል? ቃለአብ ትዝታውን ብቻ ትቶ ላይመለስ ሄዷል። መቼም ይህቺ አለም መልካም ሰው አይበረክትላትም። <ቃል!> በቆምንበት ቦታ ሁሉ ቁሜ አስብሃለሁ። በተራመድንበት መንገድ ሁሉ ስሄድ አስብሃለሁ። ልቤ ላይ ስለተቀመጥክ በምሄድበት ቦታ ሁሉ ይዤህ እዞራለሁ። ምክንያቱም እወድሃለሁ!!!

# የተመሳሳይ ጾታ ፍቅር እና አፍሪካ

የተመሳሳይ ፆታ ፍቅር ወይም የፍቅር ግንኙነት ለአፍሪካ እንግዳ ነገር ሆኖ አያውቅም፡፡ ነጮች ወደ አፍሪካ ከመምጣታቸው በፊት እና ከ ቅኝ ግዛትም በፊት ነበረ፡፡ ታዋቂ የታሪክ ምሁራን ያካሄዷቸው ጥናቶች ፣ በተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን ድርጅቶች እንዲሁም (በተለይም) በኡጋንዳው ሴክሹዋል ማይኖሪቲስ ኡጋንዳ (Sexual Minorities Uganda - SMUG) የወጡ ዘገባዎች ግብሩ/ግንኙነቱ ከምዕራባውያኑ የተገኘ ወይም የተወረሰ ሳይሆን ፣ እንዲያውም ምዕራባውያኑ አፍሪካን ከፋፍለው ከመቀራመታቸው በፊት ይገኝ እንደነበር ያወሳሉ፡፡

ኬንያዊው የታሪክ መምህር እንዳሉት “የተመሳሳይ ፆታ የፍቅር ግንኙነት ቅኝ ገዢዎች ወደ አፍሪካ ከመምጣታቸው በፊት ለረጅም ጊዜ ይገኝ እና ይተገበር ነበር፡፡”

ዓለም አቀፍ ተቃውሞን ችላ በማለት በፕሬዚዳንቷ ፊት አውራሪነት አወዛጋቢውን ፀረ-ተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት ህግ ባወጣችው ኡጋንዳ ፣ አብዛኛው ህዝቧ በተሳሳተ ሁኔታ የተመሳሳይ ፆታ ፍቅር በምዕራባውያን በተለይም በአሜሪካ የሚደገፍ እና የሚተዋወቅ ከመሆን በዘለለ ፣ በቅኝ ግዛት ጊዜ ነጮች ያስተዋወቁት ተግባር እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ሙሉ በሙሉ ስህተት ቢሆንም፡፡

በጣም ታዋቂ ከሆኑ አፍሪካውያን የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች መካከል በወቅቱ በምሥራቅ አፍሪካ በጣም የተደራጀ መንግሥት ንጉሥ  የነበሩት የዛኔዋ ቡገንዳ የአሁኗ ኡጋንዳ ንጉስ ዳግማዊ ማዋንጋ (King Mwanga II) ይገኙበታል፡፡
ከ 1884 እስከ 1888 (እ.ኤ.አ) ነግሶ የነበረው ይህ የቀድሞ የኡጋንዳ ንጉስ ከወንድ ባለሟሎቹ ጋር የፍቅር እንዲሁም የወሲብ ግንኙነት እንደነበረው በሰፊው ይነገራል፡፡ ኡጋንዳ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር የወደቀችው በ1894 መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

የጥናት ባለሞያው አምብሮስ ሙካሳ እንዲህ ብሏል፡ “ንጉስ ዳግማዊ ምዋንጋ ብዙ ወጣት ወንዶች በቤተ መንግስቱ ይኖሩ እንደነበር ፣ ለወሲባዊ ግንኙነትም ያገለግሉት እንደነበር መረጃዎች አሉ፡፡ ሚስዮናውያን ክርስትናን በሚያስተዋውቁበት ጊዜ ግን አንዳንዶቹ ወጣቶች ተጠምቀው ፣ እንዲሁም የተመሳሳይ ፆታ ወሲባዊ ግንኙነትን አስከፊነት በመማራቸው ፣ ንጉስ ምዋንጋ ከነሱ የሚያገኘውን ወሲባዊ ጥቅም መከልከል ጀመሩ፡፡”

ንጉስ ምዋንጋም ወጣት ቅምጦቹ ትዕዛዙን በመጣሳቸው ፣ እንዲሁም እንደ በፊቱ ለሱ መታዘዝ እምቢ በማለታቸው ተበሳጭቶ ከሚስዮናውያኑ ጋር ግጭት ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡ አልታዘዝ ያሉትንም እንዲገደሉ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ ከ1885 እስከ 1887 ድረስም የተቃወሙትን ሁሉ አስገድሎ ነበር፡፡ የተገደሉትም ወጣቶች ለንጉሳቸው ከመገዛት ይልቅ ለአዲሱ ኃይማኖታቸው ራሳቸውን አሳልፈው ስለሰጡ የ”ሰማዕት”ነት ማዕረግ ተሰጥቷቸው ነበር፡፡

በቡጋንዳ ግዛት “ባፌ” (Bbaffe ) ማለት “ባላችን/ባለቤታችን” ማለት ነው፡፡ በንጉስ ምዋንጋ ስር የነበሩ ሰዎች በሙሉ ፣ ወንዶቹን ጨምሮ ንጉሱን “ባፌ” (Bbaffe) በማለት እንዲጠሩት ታዘው ነበር፡፡ ወንዶችንም አግብቶ ይኖር ነበረና፡፡

“ወንዶች እንኳን ንጉስ ምዋንጋን “ባፌ” ብለው ይጠሩት ነበር። ያ ማለትም በፈለገው ጊዜ የግብረ ስጋ ግንኙነት ከነርሱ ጋር የማድረግ ሙሉ ነፃነት ነበረው ማለት ነው። ለሁሉም ወንዶች እንዲሁም ሴቶች እንደ ባል ነበረ።” - የቡጋንዳ ትልቅ ሰው ሲሞ ሙጌሬ እንደተናገሩት።


ንጉስ ዳግማዊ ምዋንጋ

SMUG በዘገባቸው፡ የወቅቱ የኡጋንዳ ፕሬዚዳንት ሙሴቬኒ በአፍሪካዊ ባህሎች ውስጥ የተመሳሳይ ፆታ ፍቅር ግንኙነቶች ይገኙ እንደነበር ያመኑበትን ንግግራቸውንም ጠቅሷል። “በማህበረሰባችን ውስጥ ጥቂት የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን ነበሩ። አይፈረድባቸውም ፣ አይገደሉም እንዲሁም አይገለሉም ነበር።” ብለዋል።

ይህም የተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት ከቅኝ ግዛት በፊት በነበረችው አፍሪካ ስለመገኘቱ ብቸኛው ማስረጃ አይደለም። በ 1606 (እ.ኤ.አ) በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ይንቀሳቀስ የነበረ የ”ኢየሱስ አማኞች ህብረት” (የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን) ቄስ እንደገለፀው “ቺባዲ (chibiadi)” የተባሉ እንደ ሴቶች የሚለብሱ ፣ እንደ ሴቶች የሚንቀሳቀሱ ወንዶች እና ወንዶች ተብለው መጠራታቸው የሚያሳፍራቸው እና የሚያስቆጣቸው ሰዎች እንደነበሩ ይገልጣል።

በ17ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አካባቢም በአሁኗ አንጎላ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ፣ ጋስፓር አዝቬሬዱች እና አንቶንዮስ ሴኩዬሪስ (Gaspar Azevereduc and Antonius Sequerius ) የተባሉ ቄሶች ፣ እንደ ሴት የሚያወሩ ፣ እንደ ሴት የሚቀመጡ እና እንደ ሴት የሚለብሱ እንዲሁም ከሌሎች ወንዶች ጋር በጋብቻ የሚጣመሩ ወንዶች አጋጥመዋቸው እንደነበረ ይናገራሉ። እነዚህ ጋብቻዎች ከመከበራቸውም ባለፈ ይሸለሙ እንደነበር ያወሳሉ።

እንደ የ90 ዓመቱ የኬንያ ቴሶ (Teso) ማህበረሰብ አዛውንት ኤጃካይት ኤሞሮት (Ejakayit Emorot) ታሪካዊ መረጃ ደግሞ ፣ እንደ ሴት በሚንቀሳቀሱ ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ባላቸው ሰዎች መሃል የተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት እንደነበር ይናገራል።

ከቅኝ ግዛት በፊት በነበረችው ቤኒን ደግሞ የተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት ወጣት ወንዶች ከሚያልፉባቸው የዕድገት ደረጃዎች ወይም ባህሪያት ውስጥ እንደ አንዱ ይቆጠር ነበር።

በአሁኖቹ ጋቦን እና ካሜሩን የሚገኙ የባንቱ ቋንቋ ተናጋሪ ፖሄይን (Pouhain ) ገበሬዎች ዘንድም የተመሳሳይ ፆታ የፍትወት ግንኙነት ‘bian nkuma’ (ቢያን ንኩማ) በመባል ይታወቅ ነበር። ይህም በወንዶች መካል የሚደረገው ፍትወታዊ የተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት ከአንዱ ወደ አንዱ እንደሚተላለፍ የሀብት መድኃኒትነት ይቆጠር ነበር።


እነዚህ ምሳሌዎች እና ብዙ ሌሎችም በብዙ አፍሪካዊ ማህበረሰቦች ዘንድ መገኘታቸው የተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት ቅኝ ገዢዎች ወደ አፍሪካ ከመምጣታቸው በፊት ለረጅም ጊዜ አፍሪካ ውስጥ ይገኝ/ይተገበር እንደነበር ያረጋግጣሉ።

የተመሳሳይ ፆታ ፍቅር ወይም ግንኙነት “አፍሪካዊ አይደለም” የሚለው ሀሳብ ግን ብዙም በመረጃ የተደገፈ አይመስልም።
አንድ ነገር ግን ግልፅ ነው፡ ዛሬ ላይ የተመሳሳይ ፆታ ፍቅር ህገወጥ በሆነባቸው የአፍሪካ ሀገራት በአብዛኞቹ ፣ ህጉ የተዋወቀው እና የተተገበረው በቅን ገዢዎች መሆኑ።

# ማንነቴን ለምን እጠላለሁ?

በቤን ዶሚነስ

ያደግነው ፣ የኖርነው ማህበረሰባዊ እና ሕብረተሰባዊ ባህሎችን ፣ ዕሴቶችን እና ሁኔታዎችን እየተማርን ነው። በዚህ በምናውቀው የተመሳሳይ ፆታ ፍቅር ጠል ፣ አባታዊ ስርዓት ተኮር እና ፆታዊ መድልዎ በተንሰራፋበት ባህል ስለ ተመሳሳይ ፆታ ፍቅር እና ማህበረሰቡ ከለመደው ወጣ ያሉ ፆታዊ ዝንባሌዎች የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን ልንሰማና ልንማር እንችላለን። በዚህም ምክንያት እኛ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያንም ሆንን የፆታ ዝንባሌአችን ከተለመደው የተለየ ሰዎች ልክ እንደማንኛውም የሕብረተሰቡ አባል ከተቃራኒ ፆታዊ ዝንባሌ የተለየ ማንነታችንን እንደ “ልክፍት” ፣ “ስህተት” ፣ “ኃጢአት “ ፣ ወይም ደግሞ “ሥነ-ምግባር የጎደለው” ነገር አድርገን ልናየው እንችላለን። ይህም ራስን ወደመጠየፍ ወይም ወደመጥላት ስሜት ይመራናል። እነዚህ ስሜቶች ደግሞ ከፍ ወዳለ ማንነትን የመጥላት “ውስጣዊ ጥላቻ”



## የዜግነት ውስጣዊ የማንነት ጥላቻ ምንድን ነው?


ውስጣዊ የማንነት ጥላቻ ወይም ጭቆና ብዙ ጊዜ የሚያጋጥው የተቃራኒ ፆታ ፍቅር ብቻ ትክክለኛው እና “ብቸኛው ፆታዊ ተማርኮ” እንደሆነ እየተማሩ እና እንዲያምኑ እየተገደዱ ባደጉት እና በሚኖሩት የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን ፣ እና ሌሎችም ከልማዱ የተለዩ ስብዕናዎች ያሏቸው ሰዎች ላይ ነው። አንዳንዴም የተቃራኒ ፆታ ተማርኮ ያላቸው ሰዎች ዘንድም ይስተዋላል። የተለያዩ ዜግነትን እና ዜጎችን በጥላቻ እና በመጥፎ የሚፈርጁ የተሳሳቱ መልዕክቶችን እና ትምህርቶችን እየሰሙ እና እየተማሩ ማደግ ይኼንን የተሳሳተ አመለካከት ወደራስ በመውሰድ ፣ ራስን ወደመጥላት ደረጃ ሊያደርስ ይችላል። በዚህም ምክንያት ብዙ የዜጋ አባላት ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚመጣ ራስን እና ማንነትን የመጥላት ፣ የሚመስለንን የመጥላት የአዕምሮ ጭንቀት ውስጥ እንዘፈቃለን።

አጠቃላይ ለማንነታችን ያለን መልካም አመለካከት ወይም ግምት እና ለግል ወሲባዊ ዝንባሌእን አዎንታዊ አመለካከት መኖር ለአዕምሮአዊ ጤናችን ወሳኝ ናቸው። አብዛኞቻችን ፣ ምናልባትም ሁላችንም በሚባል ሁኔታ ልክ እንደ አንድ ሌላ ዜጋ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ ወይም ምክንያት ዜግነታችንን ከሌሎች ፣ አልፎም ከራሳችን የደበቅንበት ጊዜ ርዝመቱ ቢለያይም ነበረ ፤ አሁንም አለ።

በተለይም የተለመዱ ከሚባሉት እንደ የወንድ ወይም የሴት የተመሳሳይ ፆታ ወሲባዊ ዝንባሌ (ጌይ ፣ ሌዝቢያን) ፣ ወይም የሁለቱም ፆታዎች ወሲባዊ ዝንባሌ (ባይሴክሹዋል) ካሉት ፆታዊ ዝንባሌዎች በዘለለ የሌሎች ተመሳሳይ ማንነቶች ግንዛቤ መጨመር እና እየተገለጡ መምጣት ፣ ቀድሞውኑ የነበረንን ራሳችንን እና ማንነታችንን ያለመፍቀድ ስሜት በተለያዩ ባህሪያት በመገለጥ ፣ ሌላውን ዜጋ ወደማጥቃት ደረጃ ሊያደርሰን ይችላል።

ራስን እና ማንነትን የመጥላት ባህሪይ በተለያዩ ከአዕምሮአዊ ጤና ጋር ተያያዥ በሆኑ መንገዶች ሊገለጥ ይችላል፡

- ፆታዊ ተማርኮን ከራስም ከሌሎችም መደበቅ ብሎም መካድ
- ፆታዊ ተማርኮን እና ማንነትን ለመለወጥ ወይም ለመቀየር መሞከር
- ምሉዕ እና በቂ የአለመሆን ስሜት መሰማት
- ሌሎች እንዲቀበሉን ከመጠን በላይ የሆነ ወይም ምንም ተነሳሽነት ማሳየት
- ለራስ ያለ ዝቅተኛ ግምት ፣ የገዛ ሰውነትን (አካልን) መጥላት
- ሌሎች ማንነታቸውን ተቀብለው ለሚኖሩ ዜጎች የሚታይ እና ግልፅ የሆነ ንቀትሌሎች ማንነታቸውን ለመቀበል በብዙ ችግር ውስጥ ለማያልፉ ዜጎች ያለ ንቀት
- የተመሳሳይ ፆታ ፍቅር ጥላቻ (homophobia) ፣ የተቃራኒ ፆታ ብቻ! ነት (heterosexism) ፣ የፆታዊ ማንነቶች ጥላቻ (Trans and Gender Non-Conforming phobia) ፣ ብሎም ፆታዊ አድልዎ (sexism ) እና ሌሎችም ችግሮች ትኩረት የሚሹ የህብረተሰቡ ችግሮች እንደሆነ አለማመን



- ለሌሎች እኛን ለማይመስሉን ፣ ወይም/እና ለሚመስሉን ያለ ንቀትና ጥላቻ ፣ አልፎ ተርፎም በሌሎች ዜጎችን በመጥላት በሚደረጉ ነገሮች እና ንግግሮች ላይ መሳተፍ
- በሌሎች የሚጠቁ ተጠቂዎች ላይ የበላይነትን ማሳየትጤነኛ ያልሆነ የፍቅር ግንኙነት ውስጥ መቆየት
- ቀጥ ወይም የተቃራኒ ፆታ አፍቃሪ መስሎ ለመታየት መሞከር ፣ አንዳንዴም ለሰዎች ስንል የተቃራኒ ፆታ ፍቅር እና ትዳር ውስጥ መግባት ፣ ወይም "ፈውስን" መመኘት
- ጓደኞቻችን ወይም ዘመዶቻችን እንዳይርቁን ክፉኛ መፍራት
- እፍረት ፣ ድብርት ፣ ንዴት ፣ ነጭናጫነት ፣ ድንጉጥ ፣ አላስፈላጊ የሆነ ራስን የመከላከል ስሜት ፣በትምህርት መዳከም ፣ ወይም ማቋረጥ ፤ በሥራ ቦታ ውጤታማነት ማነስሁልጊዜ የራስ ባህሪይን ፣ ሥርዓተኝነትን ፣ ዕምነትን ፣ አመለካከትን እና ዕይታን መቆጣጠር
- ለዜጎች መብት አቀንቃኞች ያለ አሉታዊ አመለካከት እና ነቀፌታ
- ህፃናት ደፋሪ ላለመባል ወይም ላለመምሰል ከሚመነጭ ውስጣዊ ፍርሃት ህፃናት አካባቢ ላለመሆን መፈለግ
- ደህንነቱ ያልተጠበቀ ወሲብ ማዘውተር ፣ እና ሌሎች ለኤች አይቪ እና ሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ተጋላጭ የሚያደርጉ ባህሪያትን ማሳየት
- ፍቅርን እና ወሲብን ከፆታ ጋር በማያያዝ አራርቆ የማየት ባህሪይ ፣ ስሜታዊ ቅርርብን ወይም ፍቅርን መፍራት ፣ አንዳንዴም ዝቅተኛ የሆነ የወሲብ ስሜት
- አደንዛዥ ዕፅ አብዝቶ መጠቀም ፣ መጠጥንን እና መድኃኒቶችን ጨምሮራስን ስለማጥፋት ደጋግሞ ማሰብ ፣ መሞከር ፣ እናም ራስን ማጥፋትሌሎችም.....

እኒህን እና ሌሎችም የመሳሰሉ ራስን ዜግነትን የመጥላት እና የመጨቆን አመለካከቶች እና ባህሪይያት የአንድን ሰው አዕምሮአዊ ጤና ከመበረዝ በተረፈ አስተሳሰባችንን ፣ ለሰዎች ያለንን መልካም አመለካከት ፣ ለሌሎች ያለንን ክብር ፣ ስሜቶቻችንን ፣ ዕምነታችንን እና ዕውነተኛ ማንነታችንን የመቀየር እና የመበከል ችግር አለባቸው።

ታዲያ ይኼንን ብዙዎቻችን ፈልገን ያላመጣነውን ፣ ከተማርነው ፣ ካደግንበት ፣ እና ትክክለኛ ብለን ካመንነው የተሳሳተ ባህል እና ዕሳቤ የወረስነውን ችግር በጥንቃቄ ይዘን ካላስታመምነው እና ፣ ዕውነታዎችን እና ነባራዊ ሁኔታዎችን እያጣቀስን ፣ ተሸሽገውብን የኖሩ ዕውነቶችን ፣ ዕውቀቶችን ልንመግበውና ራሳችንን ወደመቀበል በመምጣት ሕይወትን በተሻለ ሁኔታ የምናጣጥምበትን መንገድ ልንፈጥር ይገባል።

**ልክ እኛ የምናልፍበትን ዓይነት ጥያቄና የሕይወት አለመመቸትን ሌሎችም በራሳቸው መንገድ እንደሚያልፉበት መገንዘብ**

**ሰዎች አንዳችን ከአንዳችን የተለያየ የማንነት አገላለፅ ፣ ፆታዊ ተማርኮ እንዳለን መረዳት**

**ሁላችንም የተለያየ የራሳችን የሆነ ራሳችንን የመቀበል ሂደት እና ጊዜ እንዳለን ማወቅ**

**አገላለፁ እኛ ባንረዳው እና ባይገባን እንኳ ሰውን በሰውነቱ ብቻ መቀበል መቻል**

**ሁሉም ሰው የተለያየ ራሱን የመከላከያ ፣ ማንነቱን የማሳወቂያ መንገድ እንዳለው መገንዘብ**

**ስለ ፆታዊ ተማርኮ እና ማንነት የበለጠ ለማወቅ መትጋት**

የተሻለ ማህበረሰባዊ መቻቻልን ለመፍጠር እና በህብረት ለደህንነቱ የሚተጋ እና ሌሎችን በማክበር ዜግነትን በአጠቃላይ ከሚጠላው የህብረተሰብ ክፍል የሚመጣውን ጥላቻ እና ጥቃት ለመከላከል እና ግንዛቤን ለማስጨበጥ የሚተባበር ጤናማ ሕይወት ያለው ዜጋን መፍጠር እንችላለን።




# “የሌዝቢያን ፖርንማ ፀዴ ነው!”

በሴት የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን (ሌዝቢያን) ላይ ያሉ የተሳሳቱ ግንዛቤዎች

ወቅቱን አሁን በውል ባላስታውሰውም ፣ የሆነ ጊዜ ላይ ከአንድ የተቃራኒ ፆታ አፍቃሪ (ቀጥ) የሆነ የሥራ ባልደረባዬ ጋር ስለ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን (ዜግነት) የተለመደውን ኃጥያት ነው ፣ አይደለም ክርክር ገጥመን ነበር፡፡ የባልደረባዬ የመከራከሪያ ኃሳብ ከኃጥያትነት በዘለለ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ዋና ዓላማ ዘር ለመተካት በመሆኑ በሁለት ወንዶች መካከል የሚደረግ ወሲብ ኢ-ተፈጥሮአዊ እንደሆነና ለተለያዩ የጤና እክሎች እንደሚያጋልጥ የሚተነትን ነበር፡፡
ይህ ባልደረባዬ ግን በሁለት ሴቶች መካከል የሚኖርን ስሜታዊም ሆነ ወሲባዊ ቅርርብ ወይም ግንኙነትን በፅኑ ይደግፋል - የራሱን የተቃራኒ ፆታ ወሲባዊ ጥማት ስለሚያስታግስለት፡፡

**“የሌዝቢያን ፖርንማ ፀዴ ነው!” ይላል...**

ይህ የባልደረባዬ ዕይታ የእርሱ ብቻ አይደለም፡፡ ብዙዎች የሚጋሩት እንጂ፡፡

የሴት ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን (ሌዝቢያን) በተለያዩ የተመሳሳይ ፆታ ፍቅር ተቃውሞ አቀንቃኝ ሰዎች (በተለይም ወንዶች) ይህንን ወሲባዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲባል ብቻ ትኩረት የሚሰጠው በሁለተኛ ደረጃ ኃጥያትነት ነው፡፡ ምንም እንኳን የተመሳሳይ ፆታ ተማርኮ እና ሌሎች ማንነቶች የመብት ጥያቄዎች ላይ ሌዝቢያን ሴቶች በግንባር ቀደምትነት የሚገኙ ቢሆንም ፣ በአብዛኛው ህዝብ ላይ ያለው የአባታዊ ሥርዓት ተፅዕኖ ሴቶችን ከወሲብ ማርኪያነት እና ልጅ ፈልፋይነት በዘለለ ትኩረት ሳይሰጣቸው እንደነገሩ ይታለፋሉ፡፡

እስቲ ዛሬ ከላይ የጠቀስኩትን እና ሌሎች ሴት የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያን (ሌዝቢያን) ላይ ያሉ እጅግ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን በጥቂቱ እናውራባቸው ፡፡

## ሌዝቢያኖች ወንዶችን ይጠላሉ፡

የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ ሴቶች (ሌዝቢያኖች) በፆታ ከሚመስላቸው ጋር በፍቅር ስለወደቁ ብቻ ተቃራኒያቸውን ይጠላሉ ማለት መሰረት አልባ ግንዛቤ ነው። እንደማንኛውም ሰው የሚወዷቸው አሳዳጊ አባት ፣ መካሪ ወንድም ፣ አስቂኝ አጎት ፣ ታማኝ ጓደኛ አላቸው። እርግጥ ነው በሁለት ተመሳሳይ ፆታ ባላቸው ሰዎች መካከል ተፈጥሮአዊ የሆነ ልዩ ቁርኝት አለ። ያ ማለት ግን ሌሎችን ስለጠሉ ነው ማለት አይደለም።



እንዲያውም እኔ እንኳን በግሌ የማውቃቸው ሌዝቢያኖች ብዙ የወንድ ጓደኞች አሏቸው - ቀጥም ይሁን ዜጋ።

እናም ቀጦችዬ ... ጠልተዋችሁ አይደለም፤ አብረዋችሁ መተኛት ብቻ ነው የማይፈልጉት። ብዙ ልዩ የመሆን ስሜት አይሰማችሁ። ልክ እንደማንኛውም ሰው ለእነሱ እኩል ሰው ናችሁ።


vanguardngr.com

## ሌዝቢያኖች በወንድ ስለተጎዱ ፣ ወይም እድገታቸው ላይ በአባታቸው/በወንድማቸው/በአጎታቸው ስለተደፈሩ ወይም ስለተጠቁ....


አትጨርሱት። አንዲትን ቀጥ ሴት ሄዳችሁ ቀጥ የሆነችው በሴት ስለተጎዳች ፣ ወይም በእድገቷ በእናቷ ፣ በእህቷ ወይም በአክስቷ ስለተደፈረች ወይም ስለተጠቃች ወንድ አፍቃሪ መሆኗን ትጠይቃላችሁ? ... አትጠይቁም።

በዚህ ዕምነት ... እያንዳንዷ በልጅነቷ ፣ በትምህርት ቤት ፣ በቤተሰብ አባል ፣ በመንገድ ዱርዬ ፣ እንዲሁም በእናንተ የተጠቃች ሁሉ ሌዝቢያን ናት ማለት ነው?

ትናንትና መንገድ ላይ ዱርዬ ለክፏት እያለቀሰች ቤት የገባች ታናሽ እህትህ ሌዝቢያን ናት ብለህ ታምናለህ ማለት ነው?

ቀጦች ሆይ.... እመኑኝ ... ሁሉም ነገር በእናንተ ዙሪያ አይሽከረከርም። የሷ ፆታዊ ተማርኮ የራሷ ነው። ከናንተ ወንድነት ጋር ቅንጣት ታህል ቁርኝት የለውም።

## በሌዝቢያኖች የፍቅር ግንኙነት ውስጥ ማነው ወንዱ ፣ ማናት ሴቷ?



ማንም።

የሴት እና የሴት የፍቅር ግንኙነት ... እዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ወንድ የሚባል ነገር ይታያል? ... አይታይም። ፍቅር በሁለት ሰዎች .... (ሰዎች ነው ያልኩት ... ወንድ ወይም ሴት አላልኩም) መካከል የሚኖር መጣጣም እና መግባባት እንጂ አንዳቸው መሪ አንዳቸው ተመሪ የሚሆኑበት ፣ አንዳቸው አስተዳዳሪ ሌላቸው ተዳዳሪ የሚሆኑበት ... ያንን የተለመደውን አባታዊ ሥርዓት አይከተልም።

ድጋሚ ቀጦች ሆይ.... እመኑኝ ... ሁሉም ነገር በእናንተ ዙሪያ አይሽከረከርም። የሷ ፆታዊ ተማርኮ የራሷ ነው። ከናንተ ወንድነት ጋር ቅንጣት ታህል ቁርኝት የለውም።

## ሁሉም ሌዝቢያኖች ወንዳወንድ ናቸው! (?)

አሁንም ወንዶች ሆይ.... ምነው ሁሉ ነገር ከኛ ጋር ካልተቆራኘ አላችሁሳ? ወንዳወንድነት እና ሴታሴትነት ከፆታዊ ተማርኮ ጋር ምንም የሚያገናኘው ነገር የለም። ወንዳወንድም ፣ ሴታሴትም ... ወይም የሁለቱም ቅይጥ ሊሆኑ ይችላሉ። ካልተነገራችሁ አታውቁም።

ብቻ አንዲት "ወንዳወንድ" ሴት አይታችሁ ...በድፍረት "ሊሊ ነሽ ኣ!?" ብላችሁ ደም በደም አድርጋ እንዳትመልሳችሁ ተጠንቀቁ። ሃሃ



## ወንድ ውቃቢ ያደረባት ሴት ... ውቃቢዋ ሴት ስለሚፈልግ.....

በሉ... ይኼንን ባለውቃቢ ይመልስልኝ።

እናላችሁ ሴቶችዬ ... ዜጎችዬ ... ሌዝቢያኖችዬ ... ሴት የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪያንዬ ... ሊሊዎችዬ ... ምንም እያሉ ቢጠሯችሁ ... ምንም ቢሏችሁ .....
እኛ ግን ማንነታችሁ ዕውነት ፣ ፍቅራችሁም ንፁህ ፣ ቅርበታችሁም ከልብ እንደሆነ እናውቃለን!

ክበሩልን!!!!



# FAGulous!

**By: Victor Geta**:
*Is an Ethiopian queer activist who has been advocating for the physical and mental wellbeing of the Ethiopian LGBTQ+ for more than a decade.*

*Facebook: https://www.facebook.com/victorgeta*

"It was a long day and i got home late, as usual, tired. As i was sitting by the dinner table to finish up whatever was in front of me and head to bed, my only sister turned her head and said something, which led me to write all this....."i have this new nail shiner polish, do u wanna try it?...it doesn't show and it looks good." me and my sis ended up doing our nails and chit chatting late to the night.

It got me thinking, is this normal, do most guys sit on a couch and have their nails done by their sister? ...does she know, is that why she is comfortable?...does she suspect?...was it a test which i have failed so miserably?I Couldn't figure it out. It's true that we all give these little signs that we r and might be gay.

We like to cook, we like to put on that perfume which will make all heads turn, we dress nicely and neatly, and well, we walk the walk.

I call these signs, THE COMING OUT SLOWLY SIGNS. They guide people in helping them to sink the idea of our sexuality slowly. When that secret is all out at the end or one day, all they have to do is put all the signs together and it was all there at the beginning.

I was the shiny, giggly kid who tried his mom's shoe on. I was the kid in high school who carried his bag so fashionably that the girls were jealous. I was the kid who wore the freakiest clothes and wore enormous rings in campus. I am the guy who irons his clothes and shines his shoe every day to work and wears a perfume that will take over the room when i walk in the office."

These are some of the signs that i had and have. Those who know will know, those who don't, when the know one day will sit and think and say "ahaaaa ... that's why..."…. it wouldn't be that much of a surprise. Ur shiny shoe, u drinking cocktails rather than beer, u not that much addicted to soccer, your talk, your walk, you not dating women and the secret telephone conversations that u always have to take outside are all a sign. U might not know it, people may not suspect it but it's like the elephant is in the room but no one notices.

I say it's a good thing. Rather than revealing the whole thing and dropping the bomb from out of nowhere, at least the signs will give people to take u as u r and to accept. Its not like anything is going to change. Just don't wave it in their face, u might irritate some people. Don't hesitate to be yourself. It will make your life easier and it will also make their understanding way easier. Its a win win.

As for my sister, we had to agree we both looked FAGulous and went to bed.

*Victor Geta*

poetry

-my fear

I don't fear death
the thought of being
breath less don't make me cringe
I don't care if the burrow is
six feet under or sixty
I don't care about the maggots
feeding of my body
what I fear the most is
dying and not leaving a mark
without being somebody who matters

- queer citizen

I don't know how to live in this country
The county that sees me as an enemy
Like I am something
That they never heard of
The country that taught me
To hate myself and my kind
Whatever I do they can only see
What they wanna see
Not every being of me
Although it's not easy to let go
It's not just agony
It's also sweet, sweet memories.

- outsider

I was always an outsider
to my friends to my family
even to my thoughts
I was always the weird one
I can't fit in on every crowd
there was no one I could look up to
I was my own villan and my own hero.

- not alone

Now in this world love is crime
And hate is seen as a civil right
Judging someone who we never met
Is how we stand up for our beliefs
But how come we forgot
That we share this world not rule as Faros
Why don't we keep on
telling those narcissist voices
*we're not alone*
There's always someone else
We should always remind ourselves
That this is not where reap
Each other apart, this is the place
We fit every parts in the right places

***By: Yona***

# General Information...

## የጾታዊ እና ስነ ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ
## General gender and reproductive health

### Addis Alliance
www.addisalliance.org

አዲስ አሊያንስ ጤናማ እና እራሱን የሚጠብቅ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ማኅበረሰብ እንዲኖር የማድረግ ራእይን ያነገበ በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ወጣት ኢትዮጵያውያን የተመሰረተ ሀገር በቀል ማኅበር ነው።

/addisAlliance

@addis_alliance

@addis_alliance

### 1-Zega
1-Zega is a platform created in 2013 for the sharing of sexual and mental health information, as well as provision of resources and materials.

/1-zega

@1zega

## Blogs and Publications:

### Yezeginet Kibir
Queer storytelling, blogging and infotainment.

### Queer Family Ethiopia
Ethiopian Lesbian, Bisexual, Trans and queer women blogging.

## የዜጋ ድጋፍ ሰጪ ማህበራት
## Zega Support Groups

### House of Guramayle
www.houseofguramayle.org

a group of community lead activists advocating for equal access to social and economic protections and resources for the LGBTQ+ community in Ethiopia

/houseofguramayle

@houseofguramayle

### Zega Mahber
www.zegamahber.org

A USA based association aiming to bring the Ethiopian Diaspora Community together and also to support our siblings in Ethiopia.

/zegamahber

@zegamahber

@zegamahber

## Podcasts & Shows:


**Laba Podcast:** *by Addis Alliance*

**Alen Show:** *by House of Guramayle*

# UNIVERSAL HEALTH COVERAGE

## Leaving No One Behind

All UN Member States have agreed to try to achieve universal health coverage (UHC) by 2030, as part of the Sustainable Development Goals.




**Wellbeing Foundation Africa**
@wellbeingafrica

"A well-designed civil registration & vital statistics system is essential. Only with the collection and dissemination of accurate data can we ensure effective delivery, evaluation and monitoring of sustainable, effective public health strategies" @ToyinSaraki #AfricaHealth2019




Amref Health Africa and Toyin Saraki

12:24 pm · 06 Mar 19 · Twitter for Android

**IPPFAR**
@IPPFAR

'Sexual and Reproductive Health and Rights #SRHR has to be integrated into #UHC if we are to achieve on the broad Africa Health Agenda' H.E Marie-Chantal Rwakazina, Mayor, City of Kigali

#AfricaHealth2019
#AHAIC2019
#iwd2019
@Amref_Kenya

